## *ኢህአዴግና ተቃዋሚዎች በ2002 ምርጫ ምን ደገሱልን?*

*መለስ ዓ.*

- **ፕሮፌሰር በየነ ስንት ፓርቲ ይመራሉ?**
- **ሰዬና ህወሓት**

ግንቦት 15/2002 በሀገራችን በሚካሄደው 4ኛው ሀገራዊ ምርጫ ለመሳተፍ ፓርቲዎች ቅድመ-ዝግጅት ከጀመሩ የሰነባበቱ ሲሆን፣ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግም ለምርጫው ተፍ ተፍ እያለ ነው፡፡ በእስከ አሁኑ ሂደት 65 የሚሆኑ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ በመስማማታቸው ህግ ሆኖ ወጥቷል፡፡ የታዛቢዎች ምዝገባ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የመራጮች ምዝገባ ሂደቱም በተሟሟቀ ሁኔታ እንደቀጠለ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይም መድረክ የተሰኘው ጥምረት በምክንያት ላይ ሌላ ምክንያት በመደርደር ለምርጫው ማበርከት የነበረበትን አዎንታዊ አስተዋጽኦ መመልከት ይናፍቀን ጀምሯል፡፡ ይህ የመድረክ አቋም ግቡስ ምን ይሆን? የድርጅቱ መሪዎች ቃለመጠይቆች ባደረጉ ቁጥር አንዴ ጥምር መንግስት ሌላ ጊዜ ምርጫው ይራዘም እንደገና በሌላ ወቅት እኔ ያላሸነፍበት ምርጫ ዲሚክራሲያዊ አይደለም ማለት ጀምረዋል፡፡

## ***<u>የኢህአዴግ የምርጫ ግብ</u>***

በየትኛውም ሀገር በሚካሄዱ ምርጫዎች ላይ ፓርቲዎች በምርጫው የሚከተሉትን ግብ እንዲሁም ይህን ለማስፈፀም የሚጠቀሙበትን ስትራቴጂ ጥርት አድርገው ያስቀምጣሉ፡፡ የስትራቴጂው ግብ የመራጩን ይሁንታ ከሚሰጠው ድምፅ ማግኘት ነው፡፡ በሀገራችን የዲሞክራሲያዊ ምርጫ ታሪክ ሁለት አሥርት ዓመት ባይሞላውም ፓርቲዎች አለን የሚሉትን ግብ አስቀምጠው ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ገዥው ፓርቲ በመጪው ግንቦት ወር የሚካሄደውን ምርጫ በተመለከተ ያሉትን ሶስት ግቦች በድርጅቱ የንድፈ-ሃሳብ መጽሄት ቅጽ 3 ቁጥር 1 ላይ በግልፅ እንዳስቀመጠው ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ ማካሄድን ቀዳሚ ዓላማዎቹ ናቸው፡፡ የሀገሪቱ ህገ-መንግሥት በሚደነግገው መሠረት በየአምስት ዓመቱ ምርጫ ማካሄድ፣ ይህም ዲሞክራሲያዊና ሠላማዊ እንዲሆን ማረጋገጥ እንደሚገባው ገዥው ፓርቲ

ያሰምርበታል፡፡ በ1997 ከተካሄደው 3ኛው ምርጫ በኋላ በሀገራችን ተከስቶ የነበረው ሁከትና ትርምስ እንዳይደገም የማድረግ ዓላማ ይዞ እንደሚሰራም ይጠቅሳል፡፡

በሁለተኛነት የተቀመጠው ደግሞ ምርጫውን ነፃ፣ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ በማድረግ  በህዝቡ በተለይም ተቃዋሚዎችን በመረጠው ህዝብ ዘንድ ተዓማኒነትን ማስገኘት ነው፡፡ የውጭ ኃይሎች የራሳቸው ድብቅ አጀንዳ ስላላቸው ምርጫው ምንም ያህል ዲሞክራሲያዊ ቢሆን ጥላሸት የሚቀቡበት ዕድል ቢኖርም የምርጫው ተዓማኒነት በሀገራችን እየተካሄደ ያለው የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ሥር እንዲሰድ ሰላማችንም ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡ ኢህአዴግ በሶስተኛነት ያስቀመጠው ግብ ምርጫውን ዲሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊና ፍትሃዊ በማድረግ ተዓማኒነቱን ማረጋገጥ ብቻም ሳይሆን በፌዴራልና በሚወዳደርባቸው ክልሎች /ኦሮምያ፣ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦችና ትግራይ/ የአብላጫ ወንበር ማግኘት ነው፡፡

ድርጅቱ ይፋ ካደረገው ሰነድ መረዳት የሚቻለው ግቦቹ የሚነጣጠሉ ሳይሆን የሚመጋገቡ ናቸው፡፡ ገዢው ፓርቲ እነዚህን ግቦች በማስቀመጥ በቀጣዩ ምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አለን በሚሉት የምርጫ ስትራቴጂ በመንቀሳቀስ ሃሳባቸውን ለመራጩ ከመሸጥ ይልቅ ኢህአዴግን መርገም ስራቸው ሆኗል፡፡

***<u>የፖለቲካ ታላቁ ሩጫ</u>***

የመኢአድ ፕሬዝዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በቅርቡ በባህርዳር ውስጥ ከደጋፊዎቻቸው ጋር ውይይት ባደረጉት ወቅት በሀገራችን በቁጥር ከ60 በላይ ፓርቲዎች ይኑሩ እንጂ በውል እንቅስቃሴ የሚያደርጉት በጣት የሚቆጠሩ ብቻ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ ይህ የኢንጂነር ኃይሉ አስተያየት በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ብቅ ብለው በማግስቱ የሚከስሙ ፓርቲዎችን እንዲሁም በግለሰቦች ላይ የተንጠለጠሉትን ፓርቲ ተብዬዎች እንዳስብ ያስገድደኛል፡፡ በአትሌቲክሱ መስክ በታላቁ ሩጫ በዓመት አንዴ ብቅ የሚሉ ተወዳዳሪዎችን በአይነህሊናቸው አልሳላችሁም? እኔ እንደታዘብኩት ግን ታላቁ ሩጫ ሊካሄድ አንድ ሳምንት ሲቀረው ልምምድ ከሚያደርጉት፣ በውድድሩ ወቅትም ሩጫ አይሉት ዕርምጃ በሚሉት አካሄድ ከባልንጀሮቻቸው ጋር እያወጉና እየሳቁ ሜዳሊያ ለመታሰቢያነት የሚያስቀምጡ ብዙዎች ናቸው፡፡

ሌሎች ተወዳዳሪዎች ደግሞ ሥራዬ ብለው ላባቸውን ጠብ በማድረግ አሸናፊ ለመሆን ይሠራሉ።

ወደፖለቲካው ስንመጣ በሀገራችን በየአምስት ዓመቱ ምርጫ ከመካሄዱ ጋር ፓርቲዎች በምርጫ ዋዜማ ብቅ ይላሉ። ስም መጥራት ባያስፈልግም በእነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ ብዙዎቹ ከስም በስተቀር የህዝቡን ህይወት እንዲሁም የሀገሪቱን ገጽታ ሊለውጥ የሚያስችል ፕሮግራም ስለሌላቸው በምርጫው መባቻ ይሰነባጠቃሉ ወይም ይከስማሉ። የተወሰኑት ደግሞ እንደ ፓርቲ እንኳ በቀጥታ ሽንፈታቸውን በማመን ከማረምና ለቀጣዩ ውድድር ከመዘጋጀት ይልቅ በእርግማንና ዘለፋ ጊዜያቸውን ያባክናሉ።

ገዥው ፓርቲ በ1997 ምርጫ መንግሥት መመስረት ቢችልም በርካታ መራጮች በተቃውሞ ካርድ ነፍገውት ቢጫ ካርድ እንዳየ በማመን ሌላ ወገን ላይ ጣቱን ሳይቀስር ራሱን ወደመፈተሽ ነው የሄደው። ድህረ-ምርጫ 97 ተቃዋሚዎች ድምጽ የሰጣቸውን መራጭ ይሁንታ ማክበር ሲገባቸው ፓርላማ እንግባ አንግባ ሲነታረኩ፤ አዲስ አበባን የምታክል ይልቅ ከተማ አሸንፈው ከተማዋን ለማስተዳደር አሻፈረኝ አሉ። ፓርላማ ከገቡትም ውስጥ የተወሰኑት በረባ ባልረባ ምክንያት ድርድር ረግጠው ሲወጡ ተስተውለዋል።

ከባለፈው የቅንጅት ስህተት ያልተማረው መድረክ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በመደራደር በምርጫው ገንቢ አስተዋጽኦ ማድረግ ሲኖርበት ደርሶ ፍረጃ ውስጥ ገብቷል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ዛሬ በምርጫ ዝግጅት ላይ ይገኛሉ። አሁንም ኢ.ህአዴግና 65 ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ በማውጣት፣ የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በማቋቋም ቀጣዩ ምርጫ ሠላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን እየሠሩ ናቸው። በተቃራኒው መድረክ ለኢትዮጵያ ህዝቦች አለኝ የሚለውን ፕሮግራም ከማቅረብ ይልቅ ከዕለት ወደ ዕለት ምክንያቶች ይደረድራል። በቅርቡ የተከበሩ ኘሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ከግሉ ኘሬስ ጋር ባደረጉት ቃለ-መጠይቅ «የምርጫው ጊዜ ይራዘም» በሚል ፋሽን መጥተዋል። ለመሆኑ ለምርጫው መቼ ነው ዝግጅት መጀመር የነበረባችሁ? ምርጫው ከግንቦት 15 በኋላ በክረምቱ ይደረግ ቢባል አብዛኛው አርሶ አደር በሰራ በሚጠመድበት ወቅት እንዴት ይታሰባል? አቶ ስዬ አብርሀም ቢሆኑ እሳቸው ያላሸነፉበት ምርጫ ዲሞክራሲያዊ እንደማይሆን የትግራይ በተለይም የተንቤን ህዝብ ለሳቸው የተለየ ፍቅር እንዳለውና ህወሓት ከሳቸው የተሻለ ዕጩ እንደማታቀርብ

መግለፅ ጀምረዋል:: በሰዎች ላይ ከአስተያየታቸው ውጭ በግለሰቦቹ ላይ ማተኮር ባልፈልግም በአቶ ሰዬ አብረሃ የሰሞኑ ቃለ ምልልስ ላይ አንዳንድ ነገሮችን ማለት እፈልጋለሁ:: አቶ ሰዬ ከህወሓት ዕጩ ጋር ተወዳድረው አሸንፋለሁ ቢሉ ምርጫ ነውና ብዙም አይገርመኝም:: ይሁን እንጂ እኔ ያላሸነፍኩበት ምርጫ ተጭበርብሯል ወይም ዲሞክራሲያዊ አይደለም ማለታቸው ዴሞክራሲ በዋለበት እንዳልዋሉ ያሳያል::

አቶ ሰዬ የተንቤን ህዝብ የሚመርጣቸው በድርጅታቸው አንድነት/መድረክ ፕሮግራም ሳይሆን የአካባቢው ተወላጅ በመሆናቸው እንደሆነ ሲነግሩን አስበውበት ይሆን? በነገራችን ላይ አቶ ሰዬ ከልጅነት እስከ እውቀት በትጥቅ ትግሉ ለነበራቸው አስተዋጽኦ ክብር እና አድናቆት አለኝ:: ቢሆንም የትግራይ ብሎም የተንቤን ህዝብ ከህወሓት ይልቅ ለእሳቸው የተለየ ቦታ እነዳለው ሊነግሩን ግን አይገባም:: ህወሓት ውስጥ የተራራን ያህል ግዙፍ ይመስሉን የነበሩት እነ አቶ ሰዬ እንደ ራሳቸው አባባል ከድርጅቱ ውጭ የዶሮ ላባን ያህል ቀለው ስናይ እነዚህ ሰዎች በውስጠ ፓርቲ ትግል ቢያሸንፉ ኖሮ ምን ይውጠን ነበር የምንል ብዙ ወገኖች ነን:: አቶ ሰዬ የነበራቸውን መልካም ነገር ሁሉ መለኮታዊ ሳይሆን ከህወሓት እንዳገኙት ሊዘነጉ አይገባም:: አቶ ሰዬ ከህወሓት ዓላማ እና ፕሮግራም ውጭ ምንም እንዳልሆነ ገሀድ ወጥቷል::

የተንቤን ህዝብ የአካባቢው ተወላጅ የሆነው ኃይሉ ነጠበ ገና በጠዋቱ ድርጅቱን ሲከዳ ከህወሓት ጎን የታገለው ከመሪ ድርጅቱ በላይ ግለቦችን ስለማያመልክ ነው:: የድርጅቱ አሸናፊነት ሚስጥሩ ግለሰቦች ሳይሆኑ ዓላማውና ህዝቡ እንደሆኑ አያጡትም:: ለዚህም ነው ግደይም ሆኑ አቶ አረጋዊ፣ አቶ ሰዬም ሆኑ አቶ ገብሩ ሃሳባቸው ተሸፍኖ ከህወሓት ሲወጡ ድርጅቱ ከመዳከም ይልቅ በድል ላይ ድል የሚያስመዘግበው::

ህወሓት ወደ ተለያዩ ምዕራፎች እና መድረኮች ሲሸጋገር ራሱን ከወቅቱ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣመ ሲሄድ ከወየበ አመለካከታቸው ጋር የቆሙ አባሎቹን ማንገዋለል የነበረ ወደፊትም የሚኖር ሀቅ መሆኑን እነ አቶ አረጋዊ ከድርጅቱ በተለዩበት ወቅት አቶ ሰዬ መናገራቸውን አታክልቲ ሐጎስ (ለዚህ ፅሁፍ ሲባል ስማቸው ተቀይሯል) የተባሉ ጓዳቸው ገልፀውልኛል:: የማዝነው አቶ ሰዬ አዲስ ፖለቲካ ይዘው ይመጣሉ ብለው ለጠበቁት ነው:: እኔ ግን ከድርጅቱ የወጣው ቡድን አባላት «ህዝባዊ» ብለው በሰየሟት ጋዜጣ ረብ የሌለው አሉባልታ መጻፍ ሲጀምሩ እና እሷም በአጭሩ ስትቀጭ እርሜን አውጥቻለሁ:: ለነገሩ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች አይደሉ

አንዱን ፖለቲከኛ ከሌላው መለየት ያስቻሉን:: እንደ እሬት ቢ.መርም በአጠቃላይ የጊዜ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር አቶ አረጋዊ እና አቶ ሰዬ አዲስ ሃሳብና ራእይ የላቸውም:: እንደ እኔ አቶ ሰዬ ለአንድነትም ሆነ መድረክ ተጨማሪ ዕሴት ሳይሆኑ እዳ ናቸው::

## <u>*የመድረክ የምርጫ ግብ*</u>

ከተቃዋሚ ኃይሎች ውስጥ ጥቂቶቹ ለሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተገዥ ለመሆን ቆርጠው መነሳታቸውን ማረጋገጣቸው፤ የጋራ ምክር ቤት ማቋቋማቸው መጪው ምርጫ ሀገራችን የተያያዘችውን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚያጐለብት አንድ ዕርምጃ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል:: ኢህአዲግ፣ ቅንጅት፣ መኢአድ እንዲሁም ኢዴፓ ውጤቱ ምንም ሆነ ምን ሠላማዊ፣ ነፃ እና ፍትሃዊ ፖለቲካ ምርጫ ለማድረግ መስማማታቸው አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል:: አዲዮስ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ላሉ ወገኖች ዋንጫችንን አንስተናል::

በምርጫ 97 ማግስት ሁከት ተቀስቅሶ ጉዳት መድረሱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው:: በወቅቱ በዚህ ተግባር ቢሰማሩም አክሮባት ሠርተው ፓርላማ የገቡ ወገኖችና ሌሎች ፖለቲከኞች መድረክ የሚል ጥምረት መሥርተው በመንቀሳቀስ ቀጣዩ ምርጫ እንዲመክን ፍላጐት ያላቸው የሚመስል እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው:: መድረክ በቀጣዩ ምርጫ ስለማሸነፋ ዋና ግብ አድርጐ ያስቀመጠው ምርጫውን ተዓማኒነት ማሳጣት እንዲሁም አጠቃላይ ሂደቱንም ማጣጣል ነው:: ከምሥረታው ጀምሮ የተከተለው ዕርምጃ ይህን የሚያሳይ ነው:: ሮበርት ዳል የተባሉ የዲሞክራሲ ፈላስፋ Basic Dimension of Democratization contestation በሚል ርዕስ በፃፉት መፅሐፍ በአንድ ሃገር ውስጥ ለሚካሄድ ምርጫ የፖለቲካ ምህዳሩ ምቹነት እንዲሁም የፓርቲዎች አንፃራዊ አቅም ወሳኝ መሆኑን ይገልፃሉ:: የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል አልጠበበም የሚለውን የመድረክ አቋም በተመለከተ ደጋፊም ተቃዋሚም ስላለው እንዳለ ብንተወው ጥምረቱ ባለው ውስን አቅም የተነሳ በቀጣዩ ምርጫ በዴሞክራሲያዊ ውድድር እንደማያሸንፍ መሪዎቹ ያውቁታል:: ለነገሩ በድርጅቶቹ ውስጥ የታቀፉት ፖለቲከኞች ኢህአዴግ ላይ ካላቸው ኩርፊያ ውጭ ምን አንድ ያደረጋቸዋል? የሶሻል ዲሞክራሲ እና ሊብራል ዲሞክራሲ፣ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 39 የሚደግፈው ከሚቃወመው ጋር እንኳን አሸንፈው መንግሥት ሊመሰርቱ እንዴት አንድ ላይ

ይቆማሉ? በተከበሩ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እና በአንድነት መሀከል በዕጩ መረጣ ሳቢያ ያለውን የሰሞኑ እሰጣገባ ያስተውሏል፡፡

የመድረክ የምርጫ ግብ ምንጭ በ1997 ምርጫ ተግባራዊ ሊያደርገው የሞከረውና በዶ/ር ነገደ ጎበዜ የተዘጋጀው «መፀሐፈ ጉበዜ» መሆኑ ላይ ብዙ ሰዎች ይስማማሉ፡፡ የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ አይደለም በማለት በውስጥም በውጭም ውዥንብር መንዛት፣ ታፈነን፣ ደጋፊዎቻችንና ዕጩዎቻችን ታሰሩ፣ የምርጫ የምዝገባ ጊዜ ይራዘም፣ የድምጽ መስጫ ካርድ ተጭበርብሯልና ቆጠራው ትክክል አይደለም ወዘተ... በማለት ኡኡታቸውን ማሰማት፣ ይህንንም የሀገር ውስጥና የውጭ የመገናኛ ብዙሃን፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስዎች፣ የአለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ነን የሚሉ እንደ አይ.ፒ.አይ፣ ሲፒጄ፣ አርቲክል 19 ወዘተ.. የመሳሰሉ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት፣ የተለያዩ ኤምባሲዎች እንዲያስተጋቡ በማድረግ ምርጫው ነፃ አይደለም የሚል ገፅታ መሰጠት ነው፡፡

መድረክ ከቀጣዩ ምርጫ ጋር በተያያዘ ሊያስጠይቁት የሚችሉ አሳሪ የሆኑ ምንም አይነት ህጋዊ ስምምነቶች ውስጥ የመግባት ፍላጐት የለውም፡፡ ወደምርጫው በተቃረብን ቁጥር ዴሞክራሲዊና ሰላማዊ አካሄድን ከመከተል ይልቅ በምርጫው የሚሳተፉ ፓርቲዎችን እንዲሁም መሪዎቻቸውን ማሸማቀቅ፣ ማንቋሸሽና ማዋረድ ስትራቴጂው ሆኖ ብቅ እንደሚል ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ሴራራም ቻውሊያ የተባሉ ህንዳዊ የአለም አቀፍ ጉዳዮች ተመራማሪ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዲሞክራታይዜሽንና የቀለም አብዮት» በሚለው መፅሐፋቸው የቀለም አብዮቶች በባህሪያቸው ፀረ-ዲሞክራሲያዊ እንደሆኑ በአጽንኦት ይገልጿቸዋል፡፡ ዶ/ር መረራ የሚመሩት ጥምረት እያሳየ ያለውም ይህን ባህሪ ነው፡፡

መድረኮች እንደየትኞቹም የቀለም አብዮቶች እነዚህን ሁሉ ካደረጉ በኋላ ውዝግብና ንትርክ በማስነሳት ሥልጣን መያዝ ወይም መጋራት ብቸኛ አላማቸው ነው፡፡ እዚህ ላይ ኢህአዴግን ጨምሮ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማ በሠላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ተወዳድሮ ስልጣን መያዝ ነውና ይህን ቢያስቡ ችግር የለውም፡፡ ይሁን እንጂ በፕሮግራም ደረጃ ምንም ከማይቀራረቡት ኢህአዲግ ጋር ሥልጣን መጋራት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? የድርጅቱ መሪዎች ኬንያና ዚምባብዌን ለዚህ በመልካም ምሳሌነት ያነሳሉ፡፡ ለእኔ ሁለቱም ሀገሮች ሰፊ የርዕዮተ-ዓለም

እና የአመለካከት ልዩነት ያላቸው ፓርቲዎች እንዴት ሀገርን መምራት እንደማይችሉ ታላቅ አብነቶች ናቸው:: ዛኑ-ፒ-ኤፍ እና ኤም-ድ.ሲ. በዚምባቡዌ ፒ-ኤን-ዩ፣ ኦ-ዲ-ኤም እና ኦ-ዲ-ኤም-ዲ. በኬንያ እንኳን ሀገሪቱን ሊመሩ ፓርቲዎቹ በቅጡ እየተጓዙ አይደሉም::

## *አንዴ ስለመሪዎቻችን*

በውጭው ዓለም ፖለቲከኞች ለከፍተኛ የስልጣን እርከን ሲታጩ ከግል ባህሪያቸው እስከ ዙሪያ ገባቸው ይፈተሻል:: ፖለቲከኞቹ እንደተራ ሰው የሚያደርጓቸው ነገሮች ሁሉ ነውር ሆነው ይቀርባሉ:: የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ መጠጥ፣ የወቅቱ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ሲጋራ መውደድ ከምርጫው ጋር ተያይዞ ሲነሳ ነበር:: በሀገራችን የፖለቲከኞችን ገበና የሚፈትሽ ወገን ባይኖር እንኳ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው እነሱን በተመለከተ ዝምታችንን ቢያከብሩልን ምን አለበት?

መድረክ የስምንት ፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ነኝ ቢልም ከድርጅቱ መሪዎች ውጭ ብዙም የሚታይ አካል እንደሌላቸው ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ሆኖ እናሞኛችሁ አይናችሁን ጨፍኑ ይሉናል:: ይህንን ደግሞ በመረጃም በማስረጃም የተረጋገጠ ነው:: ለምሳሌ የተከበሩ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የሚመሩትን ፓርቲ (ፓርቲዎች ብንል ይቀለናል) እንመልከት:: ፕሮፌሰር በየነ የሚመሩት የሃድያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት/ሐብዴድ/ በክልል ፓርቲነት የተመዘገበ ድርጅት ነው:: ፕሮፌሰሩ ይህን ፓርቲ ይዘው የደቡብ ህብረትን መሰረትኩ ቢሉም በአሁኑ ወቅት በውስጡ ከሐብዴድ ውጭ ምንም አባል የለውም:: የደቡብ ህብረት ሲመሰረት የጌድዮ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የጉራጌ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉህዴን) የደቡብ ኦሞ ህዝብ ድርጅትን ቢይዝም ከሐብዴድ ውጭ ሶስቱም ፓርቲዎች ባይኖሩም የደቡብ ህብረት እንዳለ ቀጥሏል:: እዚህ ላይ ፕሮፌሰር በየነ በማይኖሩበት ጊዜ የፓርቲው አመራር ሆነው ብቅ የሚሉት በወላይታ ህዝብ ስም ፓርቲ ለማቋቋም ሞክረው የተውት ታዋቂው የሕግ ባለሙያ አቶ ሙሉ መጃ በየትኛው ፓርቲ ስም አባል እንደሆኑ ለብዙ ሰው ግራ ነው:: ፕሮፌሰር በየነ የእነዚህ የሌሉ ፓርቲዎች መሪ ቢሆኑም ድህረ ምርጫ የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራት ፓርቲ መሪ ሆነው ብቅ ብለዋል::

የተከበሩ ዶ/ር መረራ እና ፕሮፌሰር በየነ በፈረቃ ሲመሩት የነበረው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ወይም በተለምዶ ህብረት በሚል የምናውቀው ፓርቲ በመላው አማራ ህዝብ ድርጅት /መአህድ/ ሟቹ ቀኛዝማች ነቅአጥበብ በቀለ ሲመሩት የነበረ፣ የአገው ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስ /መጀመሪያ የተከበሩ ዶክተር መራራ አሁን የተከበሩ አቶ ቶሎሳ ተስፋዬ የሚመሩት/ የደቡብ ህብረት፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት /ኢዲዩ/ ቢመሠረትም ኢዲዩም፣ መአህድ ብሎም የአገው ህዝቦች እንደ ፓርቲ የሉም ኦብኮም ከጥምረቱ ወጥቷል ህብረቱና ፕሮፌሰር በየነ ግን ቀጥለዋል:: ይህ በምን አይነት ፖለቲካ እንደሆነ መልሱን ከራሳቸው እንጠብቃለን::

የፖለቲካ መሪዎቻችን እንኳን ለሚመሩት ህዝብ ለራሳቸው ያላቸውን ታማኝነት (ኢንቴግሪቲ) ብንጠራጠር አይፈረድብንም:: በ1992 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ለፓርላማ እጩ 5 ሺህ ለክልል ደግሞ 2500 ብር ይሰጥ በነበረበት ወቅት የተወሰነ ገንዘብ እንሰጣቹሃለን በሚል አባላቸው ያልሆኑ መንገዶችን በገንዘብ ደልለው በዕጩነት ያቀረቡ የፖለቲካ መሪዎችን የምን ጉድ ብንላቸው ይሻላል? 1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫስ ቢሆን ከምርጫ ቦርድ የተሰጣቸውን ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር... ወዘተ መርካቶ ሄደው በመሸጥ ያረጃ ገዝተው የተጠቀሙ ፓርቲዎች ነገ የመንግስት ካዝና በዕጃቸው ቢገባ ምን ሊያደርጉን እንደሚችሉ ለመተንበይ ነብይ መሆን አይገባንም::

## ***<u>የአስቴር አብዮት</u>***

ዓላማችን የተለያዩ የቀለም ስም የተሰጧቸውን አብዮቶች አስተናግዳለች:: የነጭ፣ የቀይ፣ የሃምራዊ፣ በቅርቡ ከኢራን ምርጫ በኋላ በሀገሪቱ የተፈፀመውና ምዕራባውያን አረንጓዴ አብዮት የሚሉትን አስተናግዳለች:: ድርሳናት እንደሚያመለክቱት የመጀመሪያው የቀለም አብዮት እ.ኤ.አ. በ1918 ሃንጋሪን ከኦስትሪዮ-ሃንጋሪ ለመገንጠል የተደረገው ነው:: በወቅቱ የሃንጋሪ ብሔራዊ ሶሻል ዲሞክራሲያዊ ምክር ቤት መሪ ሚሃሊ ካሮሊ ደጋፊዎች የመንግሥት መ/ቤቶችን ወረው በመያዝ ሃንጋሪን ገንጥለው የፓርቲውን መሪ ፕሬዝዳንት አደረጉ:: በዚህ ወቅት ሰልፈኞቹ የያዙት አስቴር የሚባል አበባ በመሆኑ አብዮቱ በዚህ ስም ይጠራል::

ወደ 21ኛው ክፍለ-ዘመን ስንሸጋገር ይኸው አብዮት ብርቱካንም ሆነ ሎሚ ብቻ ምንም ዓይነት የቀለም ወይንም የአትክልት ስም ይሰጠው፣ ዓላማው ለምዕራባውያን ታዛዥ የሆነ፣ የሀገሪቱን ልዕልናና ህልውና አሳልፎ የሚሰጥ መንግሥት፤ እንዲሁም እግራቸው ስር ተንበርክከው የሚሾሙና የሚሻሩ መሪዎችን ለስልጣን ማብቃት ነው:: ሳሙኤል ሀቲንግተን የተባሉ አሜሪካዊ የፖለቲካ ሳይንቲስት እ.ኤ.አ በ1991 «ሶስተኛው የዲሞክራታይዜሽን ማዕበል» በሚል ርዕስ በፃፉት መጽሐፍ ከእ.ኤ.አ 1974 በኋላ 60 የሚሆኑ የአፍሪካ፣ እስያ፣ ላቲን አሜሪካና አውሮፓ መንግስታት በድርድር፣ ተቃዋሚዎችን በግልጽ በመደገፍ እንዲሁም ጣልቃ በመግባት ምዕራባውን መለወጣቸውን ይጠቅሳሉ:: ይህ የምዕራቡ ዓለም ድርጊት በቀለም አብዮት በግልጽ ተንጸባርቋል::

የቀለም አብዮቶች የትም ተካሂዱ መቼ ዓላማቸው የእነዚህን ወገኖች የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የበላይነት ማረጋገጥ ነው:: በተለይም ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ በምሥራቅ አውሮፓና ካስፒያን ባህር ሀገሮች የተካሄዱ የቀለም አብዮቶች በአካባቢው ስትራቴጂካዊ የነዳጅ እና ጋዝ ደህንነትና የኢነርጂ ፖለቲካ ማረጋገጥ እንዲሁም ሩሲያ በአካባቢው ያላትን ተፅዕኖ በመግታት የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማስፈፀም እንደሆነም ሴራራም ቻውልያ የተባሉት ተመራማሪ ይናገራሉ:: ጆርጂያ ውስጥ ጽጌሬዳ፣ ዩክሬን ውስጥ ብርቱካናማ እንዲሁም ኪርጊስታን ውስጥ ቱሊፕ /ሃምራዊ/ ይባሉ እንጂ አላማውም፣ አፈፃፀሙም አንድ ነው:: ምዕራባዊያን ዲፕሎማቶች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በግልጽም በስውርም ያሰበስባሉ፣ አስፈላጊውንም የገንዘብና የምርጫ ባለሙያዎች ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፤ የመገናኛ ብዙሃን ከውስጥም ከውጭም ከጐናቸው እንዲቆሙ በማድረግ ተፈፀሙ የተባሉ አነስተኛ የምርጫ ችግሮችን በማራገብ ውጠረት መፍጠርና የፀጥታ መዋቅሩን በማዳከም የመከላከያ ኃይሉን በመከፋፈል አመጽ እንዲነሳ በማድረግ ለእነሱ ታማኝ የሆነ መንግስት መመስረት ነው::

አሜሪካ ለብርቱካናማው አብዮት አራማጅ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች 14 ሚሊዮን በአጠቃላይ መንግስት ለመገልበጥ እንቅስቃሴዋ ከ58-65 ሚሊዮን ዶላር ወጪ እንዳደረገች ይነገራል:: ሮን ፓውል የተባሉ የአሜሪካ ኮንግረስ አባል ይህን አሀዝ እስከ 60 ሚሊዮን ዶላር ያደርሱታል::

## *ምርጫ ወይስ ፍጥጫ*

*ገዥውም ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመጭው ምርጫ የአብላጫ መቀመጫ ያዙ ምርጫው ሠላማዊ፣ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የቤት ሥራቸውን መሥራትና በኃላፊነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ በዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር ሂደት ላይ ለምትገኘው ሀገራችን ይህ ሁኔታ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው፡፡ ሽናይደር ካርሰተን የተባሉ የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ እና ስሚተር ፊሊፕ የተባሉ የአውሮፓ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንቲስቶች በተለያዩ በሀገሮች የሚካሄዱ የዲሞክራሲ ግንባታ ስር እንዲሰዱ ገዢው ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚዎች በነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫ የሚያገኙትን ውጤት በፀጋ በመቀበል በፓርቲዎች መሀከል መተማመን እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ሁሉም የሀገራችን ፓርቲዎች ይህን ከግንዛቤ ማስገባት የግድ ይላቸዋል፡፡*

*ወደኋላ በመመለስ የተጻፈነን መቆስቆስ ባይገባም ከቀጣይ ምርጫ ጋር በተያያዘ ደም በከንቱ እንዲፈስ፣ ንብረት እንዲወድም ለየትኛውም ወገን ሊፈቀድ አይገባም፡፡ መድረክም ሆነ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዓላማቸው ምርጫ ይሁን ፍጥጫ በመግለጽ ሊነግሩን ይገባል፡፡ ወደ ምርጫው እየተቃረብን ባለንበት በአሁኑ ጊዜ መድረክ ለምርጫ እየተዘጋጀ ነው ወይስ ምርጫውን ለሁከት ሊጠቀምበት እየተሰናዳ መሆኑን የማስቀመጥ ኃላፊነት አለበት? ኤም-ቼርፍ- ባሶኒ የተባሉ የዓለም አቀፍ ህግ ባለሙያ «ድህረ-ግጭት ፍትህ» በሚል ርዕስ በፃፉት መፅሐፍ በድህረ-ምርጫ የሚፈጠሩ አለመረጋጋቶችን ፖለቲከኖች ለራሳቸው ፍላጐት ማራመጃ ሊያውሉት ስለሚችሉ ህጋዊ ዕርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ ስለሆነም ህዝቡም ሁከት ይብቃን ሊላቸው፣ መንግሥትም የተጣለበትን ሕግ የማስከበር ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡*